# የጌታችንን አምላክነት የሚያሳዩ ጥቅሶች (ለክርስቲያን አድማጭ)

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰዎች ከሚያጠቋቸው የቤተ ክርስቲያን ትምህርቶች መካከል አንዱ የጌታችን አምላክነት ነው። በታሪክም እነአርዮስ ተነሥተው የወደቁበት ጉዳይም ይኸው ርእስ ነው። በመጀመሪያ ማስረዳት የሚያስፈልገው አብዛኞቹ ክርስቲያኖች የጌታችንን አምላክነት ምሥጢረ ሥላሴንም የሚቀበሉ ናቸው። አብዛኞቹ ፕሮቴስታንቶች፣ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በሙሉ፣ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በሙሉ የጌታችንን አምላክነትና ምሥጢረ ሥላሴን የሚቀበሉ ናቸው። የጌታችንን አምላክነት የሚቃወሙት ጥቂት ፕሮቴስታንቶች ናቸው። በኢትዮጵያም ውስጥ ካሉ ፕሮቴስታንቶች almost ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ የጌታችንን አምላክነት የሚቀበሉ ናቸው። ስለዚህ ይህ ርእስ በኦርቶዶክስና በፕሮቴስታንት መካከል የሚነሣ ርእስ አይደለም። ይህ ጥያቄ ግን መጽሐፍ ቅዱስን በደንብ ላልተማሩ ለኦርቶዶክሳውያንም ለፕሮቴስታንትም አማኞች ግራ የሚያጋባ ርእስ ነው። ዳግመኛም ደግሞ ከሌሎች እምነቶችና ከእስልምና የሚመጡ ዐዳዲስ ዐማኞች ግራ መረዳት ከሚገቧቸው ነገሮች አንዱ በመሆኑ ምክንያት ይህንን መመልከት ይገባናል።

መጽሐፍ ቅዱስን እንደምልዐቱ ብንመለከት የጌታችንን አምላክነት የሚያስተምር መጽሐፍ እንደሆነ እንመለከታለን። የጌታችንን አምላክነት በመጽሐፍ ቅዱስ ከጥግ እስከ ጥግ መመልከት እንችላለን። ነገር ግን ለሰዎች ለማስረዳት ይሆን ዘንድ የጌታችንን አምላክነት የሚያሳዩ በጣም ጠንካራ ጥቅሶች አሉ። በአጭር ጊዜ ውስጥ የጌታችንን አምላክነት ለማሳየት እንዲመቻችሁ እነዚህን ጥቅሶች መጠቀም ትችላላችሁ። ጥቅሶቹ በምንም ዐይነት ወጥ አደራደር የተቀመጡ አይደሉም ፥ እናንተ በደንብ የተረዳችሁትንና በጣም አሳማኝ ነው የምትሉትን ወስዳችሁ ማዳበርና በዚያ ላይ ሥልጡን መሆን ትችላላችሁ። እንደአፍቃሪው አምላካችን እነዚህን ጥቅሶች እስኪ እንመልከታቸው፥

1) ጌታችን ይመጣል የተበለው እግዚአብሔር ነው።

/ማር 1 ፥ 1-3/

"1 የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መጀመሪያ።

2-3 እነሆ፥ መንገድህን የሚጠርግ መልክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ እያለ በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ ተብሎ በነቢዩ በኢሳይያስ እንደ ተጻፈ፥"

{ይህ ቃል በማቴዎስ ወንጌልም በሉቃስ ወንጌልም ይገኛል። ይህንን ጥቅስ በደንብ ስትረዱት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የብሉይ ኪዳኑ እግዚአብሔር (ያህዌ) እንደሆነ መመልከት ትችላላችሁ። እስኪ ከማቴዎስ ወንጌልና ከሉቃስ ወንጌል እነዚህን ጥቅሶች እንመልከት፥

/ማቴ 3 ፥ 1 - 3/

"1-2 በዚያም ወራት መጥምቁ ዮሐንስ፦ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ ብሎ በይሁዳ ምድረ በዳ እየሰበከ መጣ።

3 በነቢዩ በኢሳይያስ፦ የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ እያለ በምድረ በዳ የሚጮህ ሰው ድምፅ የተባለለት ይህ ነውና።"

/ሉቃ 3 ፥ 3 – 6/

“3-6 በነቢዩ በኢሳይያስ ቃል መጽሐፍ፦ የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ እያለ በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ፤ ዐዘቅቱ ሁሉ ይሙላ ተራራውና ኮረብታውም ሁሉ ዝቅ ይበል፥ ጠማማውም የቀና መንገድ ይሁን፥ ሸካራውም መንገድ ትክክል ይሁን፤ ሥጋም የለበሰ ሁሉ የእግዚአብሔርን ማዳን ይዩ ተብሎ እንደ ተጻፈ ለኃጢአት ስርየት የንስሐን ጥምቀት እየሰበከ በዮርዳኖስ ዙሪያ ወዳለችው አገር ሁሉ መጣ።”

[ስለዚህ በማርቆስ ወንጌልም፣ በማቴዎስ ወንጌልም፣ በሉቃስ ወንጌልም ይህ ከኢሳይያስ ትንቢት የሚገኘው ቃል ተጠቅሶ እናገኛለን። አሁን ወደዋናው ጉዳይ ከመግባታችን በፊት በዚህ ጥቅስ ውስጥ እየጮኸ የሚመጣው መልእክተኛ ማን ነው? መልእክተኛውስ የማንን መንገድ ሊጠርግ ነው የመጣው? የሚሉትን ነገሮች እንመልስ።]

ሀ) ‘መንገዱን ደልድሉ’ እያለ የሚመጣው መልእክተኛ ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ ነው።

‘መንገዱን ደልድሉ’ እያለ የሚመጣው ድምፅ ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ እንደሆነ ከራሳቸው ከወንጌላት እንመልከት፥

/ማር 1 ፥ 4 - 7/

“4 ዮሐንስ በምድረ በዳ እያጠመቀ የንስሐንም ጥምቀት ለኃጢአት ስርየት እየሰበከ መጣ።

• • •

7 ተጎንብሼ የጫማውን ጠፍር መፍታት የማይገባኝ ከእኔ የሚበረታ በኋላዬ ይመጣል።”

[ልክ ቅዱስ ማርቆስ ያንን ትንቢት ከተናገረ በኋላ መልእክተኛው ማን እንደሆነ ገለጠልን ፥ ዮሐንስ በምድረ በዳ እያጠመቀ መጣ አለን። ይህ እንዲሁ ብቻ ግጥጥም ይመስላችኋል? ወይስ ማርቆስ ሊነግረን የፈለገው ልክ ትንቢቱን ከተናገረ በኋላ እንዴት እንደተፈጸመ እያመላከተን ይሆን? ልክ ቅዱስ ማርቆስ ትንቢቱን ከተነገረ በኋላ መፈጸሙን ሲያመላክት ቀጥሎ ‘ዮሐንስ በምድረ በዳ መጣ’ ብሎ ትንቢቱ እንደተፈጸመ ነገረን። ከዚያ ደግሞ ቅዱስ ዮሐንስ ‘በኋላዬ ይመጣል’ ብሎ እየተናገረ ያለው ስለጌታችን እንደሆነ አመላከተ ማለት ነው። ከዚያ ምዕራፉን ስታነቡት ጌታችን ወደ ዮሐንስ እንደመጣ እንረዳለን። ያም ቅዱስ ዮሐንስ የተናገረለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ እንመለከታለን።

ስለዚህ እንደቅዱስ ማርቆስ ወንጌል በትንቢት የተነገረለት ይመጣል ተባለው ድምፅ ቅዱስ ዮሐንስ ፥ ድምፁ ደግሞ ሲመሰክርለት የነበረው የሚመጣው ደግሞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።]

/ማቴ 3 ፥ 1 – 3/

“1-2 በዚያም ወራት መጥምቁ ዮሐንስ፦ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ ብሎ በይሁዳ ምድረ በዳ እየሰበከ መጣ።

3 በነቢዩ በኢሳይያስ፦ የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ እያለ በምድረ በዳ የሚጮህ ሰው ድምፅ የተባለለት ይህ ነውና።”

[ቅዱስ ማቴዎስ በግልጥ ያ በኢሳይያስ ትንቢት ውስጥ የተነገረው ትንቢት ስለቅዱስ ዮሐንስ እንደሆነ ይነግረናል። ነገር ግን ያ ድምፅ ስለማን ነበር ሲመሰክር የነበረው? እስኪ እንመልከት፥]

/ማቴ 11 ፥ 10 – 11/

“10 እነሆ፥ መንገድህን በፊትህ የሚጠርግ መልክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ ተብሎ የተጻፈለት ይህ ነውና።

11 እውነት እላችኋለሁ፥ ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከመጥምቁ ዮሐንስ የሚበልጥ አልተነሣም፤ በመንግሥተ ሰማያት ግን ከሁሉ የሚያንሰው ይበልጠዋል።”

[ጌታችን ራሱ ያ በኢሳይያስ ይመጣል የተባለው ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ እንደሆነ ነገረን። ስለዚህ ምንም ጥርጥር የለውም ፥ ያ በበረሐ ሲጮህ የነበረው ድምፅ ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ ቅዱስ ዮሐንስም መንገዱን የጠረገው ከርሱ በኋላ ለመጣው ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ነው ማለት ነው።]

/ሉቃ 3 ፥ 2 – 6/

“2 ሐናና ቀያፋም ሊቃነ ካህናት ሳሉ፥ የእግዚአብሔር ቃል ወደ ዘካርያስ ልጅ ወደ ዮሐንስ በምድረ በዳ መጣ።

3-6 በነቢዩ በኢሳይያስ ቃል መጽሐፍ፦ የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ እያለ በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ፤ ዐዘቅቱ ሁሉ ይሙላ ተራራውና ኮረብታውም ሁሉ ዝቅ ይበል፥ ጠማማውም የቀና መንገድ ይሁን፥ ሸካራውም መንገድ ትክክል ይሁን፤ ሥጋም የለበሰ ሁሉ የእግዚአብሔርን ማዳን ይዩ ተብሎ እንደ ተጻፈ ለኃጢአት ስርየት የንስሐን ጥምቀት እየሰበከ በዮርዳኖስ ዙሪያ ወዳለችው አገር ሁሉ መጣ።”

/ሉቃ 7 ፥ 27 – 28/

“27 እነሆ፥ መንገድህን በፊትህ የሚጠርግ መልክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ ተብሎ የተጻፈለት ይህ ነው።

28 እላችኋለሁ፥ ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከመጥምቁ ዮሐንስ የሚበልጥ ማንም የለም፤ በእግዚአብሔር መንግሥት ግን ከሁሉ የሚያንሰው ይበልጠዋል።”

[በቅዱስ ሉቃስ በወንጌልም ቢሆን ያ የሚመጣው ድምፅ ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ እንደሆነ ፥ እርሱ መንገዱን የሚጠርገው ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ መመልከት ይቻላል። አሁን ይህ ከኢሳይያስ የተጠቀሰው ትንቢት ምን እንደሆነ እንመልከት፥]

ለ) በወንጌላቱ ላይ የተጠቀሰው ትንቢት የትኛው ትንቢት ነው?

በእነዚህ ወንጌላት ላይ የተጠቀሰው ዋነኛው ጥቅስ ከኢሳይያስ ትንቢት ነው ፥ ነገር ግን የኢሳይያስን ትንቢት ሌላም ቦታ ላይ ደግመን እናገኘዋለን። ሁለቱን ትንቢታት እስኪ እንመልከታቸውን የሚያመላክቱትን እንመልከት፥

/ኢሳ 40 ፥ 3 – 5/

“3 የአዋጅ ነጋሪ ቃል፦ የእግዚአብሔርን መንገድ በምድረ በዳ ጥረጉ፥ ለአምላካችንም ጐዳና በበረሀ አስተካክሉ።

4 ሸለቆው ሁሉ ከፍ ይላል፥ ተራራውና ኮረብታውም ሁሉ ዝቅ ይላል፤ ጠማማውም ይቃናል፥ ስርጓጉጡም ሜዳ ይሆናል፤

5 የእግዚአብሔርም ክብር ይገለጣል፥ ሥጋ ለባሹም ሁሉ በአንድነት ያየዋል፥ የእግዚአብሔር አፍ ይህን ተናግሮአልና”

/ሚል 3 ፥ 1/

“እነሆ፥ መልእክተኛዬን እልካለሁ፥ መንገድንም በፊቴ ያስተካክላል፤ እናንተም የምትፈልጉት ጌታ በድንገት ወደ መቅደሱ ይመጣል፤ የምትወዱትም የቃል ኪዳን መልእክተኛ፥ እነሆ፥ ይመጣል፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።”

[በኢሳ 40 ፥ 3 ላይ ያለው የአዋጅ ነጋሪ ቃል ለማን ነው መንገዱን ጥረጉ እያለ ያለው? መንገዱን ጥረጉ ብሎ ‘እግዚአብሔር’ ይመጣል ብሎ ነገረን። ለዚያ ነው ‘የእግዚአብሔርን መንገድ በምድረ በዳ ጥረጉ፥ ለአምላካችንም ጐዳና በበረሀ አስተካክሉ።’ እያለ እየተናገረ ያለው። በሚል 3 ፥ 1 ላይም ራሱን ነገር ነው የምንመለከተው ፥ እግዚአብሔር እንዲህ አለ ‘ “እነሆ፥ መልእክተኛዬን እልካለሁ፥ መንገድንም በፊቴ ያስተካክላል።’ ስለዚህ ከእነዚህ ትንቢቶች በግልጥ እንደምንረዳው በምድረ በዳ የተላከው ድምፅ መንገዱን እየጠረገ ያለው ለአምላካችን ለእግዚአብሔር (ያህዌ) ነው ማለት ነው።]

ሐ) አሁን ይህ ወሳኝነቱ ምንድን ነው?

በትንቢተ ኢሳይያስና በትንቢተ ሚልክያስ እንደተመለከትነው በምድረ በዳ የሚጮኸው ድምፅ መንገዱን እየጠረገ ያለው መንገዱን እያስተካከል ያለው ለአምላካችን እግዚአብሔር ነው። በወንጌላቱ ደግሞ ያ በምድረ በዳ የሚጮኸው ድምፅ ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ እንደሆነ ተነግሮናል። አሁን ምን እያመላከተን እንደሆነ ተመልከቱ።

በምድረ በዳ የሚጮኸው ድምፅ እንደኢሳይያስና እንደሚልክያስ አስተምህሮ መንገዱን እየጠረገ ያለው ለእግዚአብሔር ነዋ? ‘አዎን’ በወንጌላት ደግሞ ያ ድምፅ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ እንደሆነ ነግሮናል አይደል? ‘አዎን’ ቅዱስ ዮሐንስ ደግሞ መንገዱን እየጠረገ ያለው ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው አይደል? ‘አዎን’ ስለዚህ ቅዱስ ዮሐንስ (በምድረ በዳ የሚጮኸው ድምፅ) መንገዱን እያስተካከለ ያለው እግዚአብሔር ለሆነው ለጌታችን ለኢዩስ ክርስቶስ ነው ማለት ነው። ስለዚህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያ በብሉይ ኪዳን እመጣለሁኝ ያለው እግዚአብሔር ነው ማለት ነው። ደግሞ የሚደንቀው ወንጌላቱ ሁሉ ገና ከመጀመራቸው የጌታችንን አምላክነት ተናግረው መጀመራቸው ነው። ቅዱስ ዮሐንስ ደግሞ ያንን በግልጥ ቃል ‘በመጀመሪያ ቃል ነበረ፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበር’ ብሎ ነገረን። አያችሁ? አራቱም ወንጌላት ገና ከመጀመራቸው የጌታችንን ፍጹም አምላክነት አስተምረው ይጀምራሉ። አያችሁ የወንጌላቱ መሰናሰል? ምን ዐይነት ተመሳሳይ የሆነ ውብ መልእክት እንደሚያስተላልፉ?

ስለዚህ ከዚህ በኋላ በጣም በቀላሉ ከማቴዎስ ከተባላችሁ ከማቴዎስ፣ ከማርቆስ ከተባላችሁ ከማርቆስ፣ ከሉቃስ ከተባላችሁ ከሉቃስ ከዮሐንስ ከተባላችሁ ከዮሐንስ ወንጌል በቀላሉ ማሳየት ትችላላችሁ ማለት ነው። ይህንን አምላክነቱን ከጫፍ እስከጫፍ የሚያስተምር ቅዱስ መጽሐፍን የሰጠን የክብር ባለቤት ኢየሱስ ክርስቶስ ስሙ ለዘለዓለሙ የገነነ ይሁን።}

ይህንን ጥቅስ ለመመለስ ሰዎች እንዲህ ለማለት ይሞክራሉ “በኢሳይያስና በሚልክያስ ትንቢት ላይ እግዚአብሔር እየተባለ የሚጠራው የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነው እንጂ ቃል በቃል እግዚአብሔር አይደለም። ምክንያቱም በመጽሐፍ ቅዱስም አንድ ሰው ሌላ ሰውን ልኮ መልእክት ቢያደርስ ያ ራሱ ሰውዬ መልእክት አደረሰ ይባላልና። ለምሳሌ ፥ አበበ እኅቱ

ሰላምን ወደ ጓደኛው ከበደ ቢልክ በመጽሐፍ ቅዱስ ባሕል አበበ ወደ ከበደ ሄዶ መልእክቱን ተናገረ ማለት ይቻላልና።" ይህ መንገድ በኢሳይያስና በሚልክያስ ትንቢት ላይ እንደማይሠራ እናሳይ። እስኪ ጥቅሱን መልሰን እንመልከተው፥

/ኢሳ 40 ፥ 3 - 5/

"3 የአዋጅ ነጋሪ ቃል፦ የእግዚአብሔርን መንገድ በምድረ በዳ ጥረጉ፥ ለአምላካችንም ጐዳና በበረሀ አስተካክሉ።

4 ሸለቆው ሁሉ ከፍ ይላል፥ ተራራውና ኮረብታውም ሁሉ ዝቅ ይላል፤ ጠማማውም ይቃናል፥ ስርጓጕጡም ሜዳ ይሆናል፤

5 የእግዚአብሔርም ክብር ይገለጣል፥ ሥጋ ለባሹም ሁሉ በአንድነት ያየዋል፥ የእግዚአብሔር አፍ ይህን ተናግሮአልና"

{የአዋጅ ነጋሪ ቃል የተባለው ለእግዚአብሔር መልእክተኛው ነው። እንደነዚህ ሰዎች አተረጓጐም ደግሞ እዚህ ጋር እግዚአብሔር የተባለው የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነው። እስኪ ጥያቄ እንጠይቅ ፥ 'የአዋጅ ነጋሪ ቃል የተባለው የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነው ፥ እግዚአብሔር የተባለው ደግሞ ራሱ ሌላ የእግዚብሔር መልእክተኛ ነው። ስለዚህ የአዋጅ ነጋሪ ቃል የተባለው የእግዚአብሔር መልእክተኛ ከሆነ እዚህም ጋር 'እግዚአብሔር' ተብሎ መጠራት ይችላል ማለት ነው። እንደነዚህ ሰዎች አካሄድ ከሆነ ለምንድን ነው የመጀመሪያው መልእክተኛ እግዚአብሔር ሳይባል ሁለተኛው መልእክተኛ እግዚአብሔር የሚባለው? አያችሁ ጥቅሱን እንዴት ግራ እንደምታጋቡት በዚህ ዐይነት አካሄድ። ይህ የአተረጓጐም መንገድ ምንኛ ጥቅሱን እንደሚያበላሸው አያችሁ? እንደነዚህ ሰዎች ፍልስፍና 'የመጀመሪያው መልእክተኛ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ሆኖ ሳለ እግዚአብሔር ተብሎ አልተጠራም ፥ ነገር ግን ሁለተኛው መልእክተኛ እንደመጀመሪያው መልእክተኛ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ሆኖ ሳለ እርሱ ብቻውን እግዚአብሔር ተባለ።' በጣም አሳማኝ የትርጓሜ መንገድ ነው ባካችሁን?

ደግሞም ኢሳይያስ 'እግዚአብሔር ብቻ' ብሎ አያበቃም። 'ለአምላካችንም' ብሎ ያጸናዋል። ስለዚህ እንደነዚህ Eisteinኦች አካሄድ የእግዚአብሔር መልእክተኛ የሆነ ሰው 'አምላካችን' ተብሎ ሊጠራ ይችላል ማለት ነው። ስለዚህ ሐዋርያት የእግዚአብሔር መልእክተኛ እንደመሆናቸው 'አምላኮቻችን' ብለን መጥራት እንችላለን ማለት ነው። ቅዱስ ጳውሎስ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ስለነበረ 'አምላኬ' ብዬ መጥራት እችላለሁኝ ማለት ነው። አያችሁት ምን ዐይነት አስቂኝ የትርጓሜ መንገድ ፥ አሳዛኝ የመጽሐፍ ቅዱስ ቡጨቃ እንደሆነ? ስለዚህ ይህንን ጥቅስ እንደዚህ መተርጐም የመጽሐፍ ቅዱስን አተረጓጐም በሙሉ ማበላሸት ነውና ይህ የመልስ ሙከራ አይሠራም።}

2) ጌታችን ከቶማስ 'አምላኬ መባልን ተቀብሏል'

/ዮሐ 20 ፥ 27 - 29/

"27 ከዚያም በኋላ ቶማስን፦ ጣትህን ወደዚህ አምጣና እጆቼን እይ፤ እጅህንም አምጣና በጎኔ አግባው፤ ያመንህ እንጂ ያላመንህ አትሁን አለው።

28 ቶማስም፦ ጌታዬ አምላኬም ብሎ መለሰለት።

29 ኢየሱስም፦ ስለ አየኸኝ አምነሃል፤ ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው አለው።"

{አንድ አማኝ የሆነ አይሁዳዊ ሰው ሌላ ፍጡርን በየትኛውም መንገድ 'አምላኬ' ብሎ ሊጠራው አይችልም። በብሉይ ኪዳን ውስጥ አንድም ቦታ ቢሆን ሰው ሌላ ፍጡርን 'አምላኬ' ብሎ ሊጠራው አይችልም። ካለ እስኪ ፈልጉና አምጡት ፥ ነገር

ግን ያልኳችሁን አስተውሉ። ያልኳችሁ ‘አምላኬ’ ብሎ አንድ ከአሕዛብ ያልሆነ እግዚአብሔርን በጽድቅ የሚከተል ሰው ለሌላ ፍጡር ሲናገር እንጂ እግዚአብሔር ለሙሴ ‘በፈርዖን ላይ አምላክ አርጌሃለሁኝ’ እንዳለው ያለ አይደለም። ይህ ዐይነት ጥቅስ የማይሆነው ምክንያቱ አንደኛ ፈርዖን ሙሴን ‘አምላኬ’ አላለውም ፥ ዳግመኛም እግዚአብሔር ለሙሴ እያለው ያለው ‘ያለፈቃዱም ቢሆን ትገዛው አምላክ አድርጌሃለሁኝ’ ብሎ ነው እንጂ ፈርዖን በፈቃዱ አይደለም ሙሴን ‘አምላኬ’ እያለው ያለው። በመጨረሻም ደግሞ ፈርዖን እግዚአብሔርን የማያውቅ ከአሕዛብ ወገን ነው። ስለዚህ እስኪ ያልኳችሁን ፈልጉና አምጡ።

አይሁዳዊ የሆነ አንድ እግዚአብሔር እንዳለ የሚያምን ቶማስ ጌታችንን ‘አምላኬ’ ብሎ ሲጠራው ያ ራሱ እግዚአብሔር ነህ እያለው መሆኑን መመልከት ይገባል። ጌታችን ቶማስ እንዳለው እግዚአብሔር ባይሆን ኖሮ ፈጥኖ ቶማስን መገሠጽ ይገባው ነበር። ምክንያቱም ፍጡርን ‘እግዚአብሔር ነህ’ ብሎ መጥራት እግዚአብሔር ላይ ሌላ አምላክ ማምለክ ነውና። ከዐሠርቱ ትእዛዛት የመጀመሪያውን መተላለፍ ነው ፥ ነገር ግን ጌታችን ምን ብሎ እንደመለሰለት ተመልከቱ። “ኢየሱስም፦ ስለ አየኸኝ አምነሃል፤ ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው አለው።” ምን??? ጌታችን ይህንን የቶማስ ንግግር ተቀበለው ማለት ነው? እዚህ ጋር መረዳት የሚገባን ሁለት አማራጭ እንዳለን ነው ፥ ወይ ጌታችን እውነት አምላክ መሆኑን ነው። ወይም ደግሞ ይህንን በመቀበል አምላክን የሚሳደብ ቀጣፊ ነበር። የትኛውም ክርስቲያን ሁለተኛውን ሊመርጥ አይችልም ፥ ስለዚህ ያለን አማራጭ የመጀመሪያው ነው። ጌታችን እውነተኛው እግዚአብሔር ነው።}

ይህንን ጥቅስ ለመመለስ ከሚሞከርባቸው መንገዶች መካከል ያሉትን እንመልከት፥

ሀ) ቶማስ ‘ጌታዬ’ ሲል ጌታችንን ፥ ‘አምላኬ’ ሲል ደግሞ በርሱ ያደረውን አብን ነው።

ይህ መንገድ አንድ ሰው ሊሄድበት የሚችለው በጣም ሞኙ መንገድ ነው ብዬ አስባለሁኝ። ስለዚህ ጌታችንን ‘አምላኬ’ ሲለው ጌታችንን ራሱን ሳይሆን በርሱ ያደረውን ‘አብን’ ነው ማለት ነው። እስኪ ይህንን ራሱን መንገድ ተጠቅሜ ሌሎች ጥቅሶችን ልመልከታቸው።

/ዮሐ 14 ፥ 17/

“17 እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለ ሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው፤ ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር በውሥጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ።”

{እዚህ ጋር ጌታችን ለሐዋርያቱ መንፈስ ቅዱስን ታውቁታላችሁ ፥ እርሱ በውስጣችሁም ስለሚሆን እያለ እየነገራቸው ነው። ስለዚህ በሐዋርያቱ ላይ መንፈስ ቅዱስ አድሮባቸዋል ማለት ነው። ስለዚህ እኔ ቅዱስ ጴጥሮስን ‘መንፈስ ቅዱስ ሆይ’ እያልሁኝ መጥራት እችላለሁኝ ፥ ምክንያቱም እኔ እያልሁኝ ያለሁት ጴጥሮስን ሳይሆን በውስጡ ያደረውን መንፈስ ቅዱስን በመሆኑ ምክንያት።}

/ዮሐ 14 ፥ 23/

“23 ኢየሱስም መለሰ አለውም፦ የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል ወደ እርሱም እንመጣለን በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን።”

{ስለዚህ አማኞችን በሙሉ ‘አምላኬ’ እያልሁኝ መጥራት እችላለሁኝ ማለት ነው። ምክንያቱም አብ ስለሚያድርባቸው ማለት ነው። ስለዚህ ወንድሞቼንና እኅቶቼን አምላኮቼ እያልሁኝ ብጠራቸው ችግር የለውም ፥ ምክንያቱም እያሉት ያለሁት ለእነርሱ ሳይሆን በውስጣቸው ላደረው ከአብ በመሆኑ ምክንያት። አያችሁት አንድ ሰው መጽሐፍ ቅዱስን እንደምልዐቱ ካልተመለከተ የሚፈጠረውን? መጽሐፍ ቅዱስን አዛብቶ ያርፈዋል።}

ለ) ‘ጌታዬ’ ብሎ ጌታችንን አመሰገነ ፥ ‘አምላኬ’ ብሎ ደግሞ አብን አመሰገነ።

ይህ ትንሽ ከቀደመው የሚለየው እኒህ የሚሉት ‘አምላኬ’ ብሎ የጠራው ጌታችንን አይደለም ፥ ይልቁንም አብን እየጠራ ነው እንጂ ማለታቸው ነው። የቀደሙት ያሉት ‘ቶማስ ጌታችንን አምላኬ ብሎታል ፥ ያለው ግን በውስጡ አብ በማደሩ እንጂ እርሱ አምላክ በመሆኑ ምክንያት አይደለም።’ ነበር። የአሁኖቹ ደግሞ ‘ቶማስ ጌታችንን አምላኬ ብሎ አልጠራውም ፥ ይልቁንም ጌታዬ ሲል ጌታችንን አምላኬ ሲል ደግሞ ጌታችንን ሳይሆን አብን ነው’ ይላሉ።

ስለዚህ ከእነዚህ ሰዎች ጋር ክርክሩ የሚኖረው ‘አምላኬ’ የሚለው ቃል ለጌታችን ነው ወይስ ለጌታችን አይደለም የሚለው ላይ ነው። ይህንን ለመርታት በቀላሉ ወደ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌል ጥንታዊ ቋንቋ በመሄድ መርታት ይቻላል። የቅዱስ ዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 20 ቁጥር 28 እንዲህ ይላል።

/ዮሐ 20 ፥ 28/

“”

{በግሪኩ ላይ κύριός μου(ኪሪዩስ ሙ) የሚለው ቃል ‘ጌታዬ’ የሚለውን ቃል ፥ Θεός μου(ቴዩስ ሙ) የሚለው ቃል ‘አምላኬ’ የሚለውን ቃል የሚወክለው ነው። አሁን Θεός μου የሚለው ቃል Θεέ μου ብሎ ቢጻፍ ኖሮ ወደሌላ አካል እያመላከተ እንደሆነ እንገምት ነበር ፥ Θεός μου ብሎ በመጻፉ ግን κύριός μου ጋር አንድ የሆነ አካልን እያመላከተ እንደሆነ እናውቃለን። ያ ደግሞ ሁለቱም እያመላከቱ ያሉት ሁለት ቃላት እርሱ የተባለውን (ማለትም ጌታችንን) ነው። ስለዚህ ይህንን ራሱን ግሪክ በሌላ ግልጥ በሆነው መንገድ እንተርጒመው ብንል ፥ ‘የእኔ ጌታና አምላክ’ ይሆናል ማለት ነው። ምናልባት ይህ ጥቂት ግራ የሚያጋባ ይመስለኛል ፥ ነገር ግን ይህንን በደንብ መረዳት ለምትፈልጉ ሰዎች የMurray J. Harrisን *John: Exegetical Guide to the Greek New Testament* የሚለውን መጽሐፍ መመልከት ይቻላል።}

ሐ) ቶማስ ይህንን የተናገረው በድንጋጤ ምክንያት ነው ፥ ስለዚህ አስቦበት አይደለም።

ይህንን መርታት በጣም ቀላል ነው ፥ ምክንያቱም እንዳሉት ቢሆን ኖሮ ጌታችን ቶማስን ይገሥጸው ነበር። ጌታችን ቶማስን ባለመገሠጹ ምክንያት ያንን የቶማስ ንግግር እንደተቀበለው እንመለከታለን። ምክንያቱም ይህ የተፈጠመባቸው ሐዋርያት ይህ ዐይነት ንግግር ሲደረግላቸው እንዴት እንደመለሱ እንመልከት፥

/ሐዋ 14 ፥ 11 - 15/

“11 ሕዝቡም ጳውሎስ ያደረገውን ባዩ ጊዜ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በሊቃኦንያ ቋንቋ፦ አማልክት ሰዎችን መስለው ወደ እኛ ወርደዋል አሉ፤

12 በርናባስንም ድያ አሉት፤ ጳውሎስንም እርሱ በመናገር ዋና ስለ ነበረ ሄርሜን አሉት።

13 በከተማውም ፊት ቤተ መቅደስ ያለው የድያ ካህን ኮርማዎችንና የአበባን አክሊሎች ወደ ደጃፍ አምጥቶ ከሕዝቡ ጋር ሆኖ ሊሠዋላቸው ወደደ።

14 ሐዋርያት በርናባስና ጳውሎስ ግን ይህን በሰሙ ጊዜ ልብሳቸውን ቀደው ወደ ሕዝቡ መካከል እየጮኹ ሮጡ፥

15 እንዲህም አሉ፦ እናንተ ሰዎች፥ ይህን ስለ ምን ታደርጋላችሁ? እኛ ደግሞ እንደ እናንተ የምንሰማ ሰዎች ነን፥ ከዚህም ከንቱ ነገር ሰማይንና ምድርን ባሕርንም በእነርሱም ያለውን ሁሉ ወደ ፈጠረ ወደ ሕያው እግዚአብሔር ዘወር ትሉ ዘንድ ወንጌልን እንሰብካለን።”

{ልክ ቅዱስ ጳውሎስና ቅዱስ በርናባስ አማልክት ተብለው ሲጠሩ ምን ያህል እንደተቃወሙት ተመለከታችሁ? ይህንን መቀበል ማለት ታላቂቱን ትእዛዝ መሻር ሰውም ያንን እንዲሸር ማድረግ ነውና ይህንን በጽኑ ተቃወሙት ፥ ጌታችንን ግን እንዳልተቃወመው ተመልከቱ። አያችሁ? ጌታችንን ያንን በመቀበሉ ምክንያት ፍጹም አምላክ እንደሆነ ነገረን ማለት ነው።}

3) እግዚአብሔር አብ ወልድን ‘እግዚአብሔር ሆይ’ እያለ ጠርቶታል።

ይህ ጥቅስ በአንድ ድንጋይ ብዙ ወፎችን ለመምታት ይጠቅማል። ሰዎች ‘ጌታችን አምላክ ከሆነ እንዴት ወደ አብ ይጸልያል’ ይላሉ። መልሳችንም ‘እንደ ክርስትና አስተምህሮ መጸለይ ማለት መጠየቅ፣ ማናገር ማለት ነው እንጂ ማምለክ ማለት አይደለም’ ነው። ይህንን ደግሞ ከሚያሳዩልን ጥቅሶች መካከል እግዚአብሔር አብም ወደ ወልድ መጸለዩ ነው። ይህንን በዕብ 1 ፥ 8 ላይ የምንመለከተው ነው።

/ዕብ 1 ፥ 8 - 12/

“8 ስለ ልጁ ግን፦ አምላክ ሆይ፥ ዙፋንህ እስከ ዘላለም ድረስ ይኖራል፤ የመንግሥትህ በትር የቅንነት በትር ነው።

9 ጽድቅን ወደድህ ዓመፅንም ጠላህ፤ ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክህ ከጓደኞችህ ይልቅ በደስታ ዘይት ቀባህ ይላል።

10 ደግሞ፦ ጌታ ሆይ፥ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ፥ ሰማዮችም የእጆችህ ሥራ ናቸው፤

11 እነርሱም ይጠፋሉ አንተ ግን ጸንተህ ትኖራለህ፤ ሁሉም እንደ ልብስ ያረጃሉ፥

12 እንደ መጎናጸፊያም ትጠቀልላቸዋለህ ይለወጡማል፤ አንተ ግን አንተ ነህ፥ ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም ይላል።”

{አብ ለልጁ ‘አምላክ ሆይ ፥ ዙፋንህ እስከ ዘለዓለም ድረስ ይኖራል’ ብሎ ወደ እርሱ ጸለየ። ሰዎች እንደሚሉት መጸለይ ማለት ማምለክ ከሆነ አብ አምላክ አይደለም ወልድ ብቻውን አምላክ ሆነ ማለት ነው። እኒህን ሰዎች በቀላሉ ለመርታት ይህንን ጥቅስ መጠቀም ይቻላል። ነገር ግን በተጨማሪም ደግሞ የጌታችን የአምላካችን የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት በግልጥ ከሚያሳዩ ጥቅሶች መካከል አንዱ ይህ ነው። እግዚአብሔር አብ ለእግዚአብሔር ወልድ ሲያናግር የጠቀሰው መዝ 45 ፥ 6-7 እና መዝ 102 ፥ 25 — 27ን ነው። እስኪ እኒህን ጥቅሶች ተመልክተን እንመለስ፥

/መዝ 45 ፥ 6-7/

“6 አምላክ ሆይ፥ ዙፋንህ ለዘላለም ነው፤ የመንግሥትህ በትር የቅንነት በትር ነው።

7 ጽድቅን ወደድህ ዓመፃንም ጠላህ፤ ስለዚህ ከባልንጀሮችህ ይልቅ እግዚአብሔር አምላክ የደስታ ዘይትን ቀባህ።”

/መዝ 102 ፥ 25 – 27/

“25 አቤቱ፥ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ፥ ሰማያትም የእጅህ ሥራ ናቸው።

26 እነርሱ ይጠፋሉ፥ አንተ ግን ትኖራለህ፤ ሁላቸው እንደ ልብስ ያረጃሉ፥ እንደ መጐናጸፊያም ትለውጣቸዋለህ፥ ይለወጡማል፤

27 አንተ ግን ያው አንተ ነህ፥ ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም።”

[ቅዱስ ዳዊት ለእግዚአብሔር የጸለየውን ጸሎት እግዚአብሔር አብ ለጌታችን ጸለየው። በዚያውም ምን እያለ ጠራው? ‘አምላክ ሆይ’ ፣ ‘ጌታ ሆይ’ እያለ ከአብ ጋር በአንድነት የብሉይ ኪዳኑ እግዚአብሔር መሆኑን ገለጠልን። ይህ ጥቅስ ‘ፈጥሮ ፈጠረበት’ የሚሉትን አርዮሳውያንን ራሱ ያጠፋቸዋል። ‘ሰማዮች የእጆችህ ሥራዎች ናቸው’ ብሎ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በወልድ በኩል ዓለምን መፍጠራቸውን ያመላክታልና። ወልድም በፈቃዱ ዓለማትን እንደፈጠረ ፥ እንዲሁ መጣሪያ ብቻ እንዳልነበረ ይህ ጥቅስ ያሳየናል። ይህ ጥቅስ እንዴት እንሚመለጥ አላውቅም ፥ ምክንያቱም የመዝሙረ ዳዊት ላይ በዕብራይስጡ ያለውንም ስንመለከት ለማንኛውም ፍጡር የማይሰጠው የእግዚአብሔር ልዩ ስሙ ‘ያህዌ’ ይገኛልና። ይህ ጥቅስ በግልጥ እግዚአብሔር ወልድ አምላክ እንደሆነ ሲያመላክተን ነው።] }

4) ጌታችን ፍጥረትን ሁሉ የፈጠረው ፈጣሪ ነው

በብሉይ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር ብቻውን ፍጥረትን ሁሉ እንደፈጠረ ይነግረናል። ይህንንም በትንቢተ ኢሳይያስ ላይ እንመለከተዋለን፥

/ኢሳ 44 ፥ 24/

“24 ከማኅፀን የሠራህ፥ የሚቤዥህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ሁሉን የፈጠርሁ፥ ሰማያትን ለብቻዬ የዘረጋሁ ምድርንም ያጸናሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ ከእኔ ጋር ማን ነበረ?”

{እግዚአብሔር ብቻውን ሁሉንም ነገር ፈጠረ። ማንም ከእርሱ ጋር እንዳልነበረ ነገረን። ነገር ግን በብሉይ ኪዳን ውስጥ ራሱ እስኪ ፍጥረትን የፈጠሩ ማን ማን እንደሆኑ እንመልከት፥}

/ኤር 1 ፥ 4 - 8/

“4 የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ።

5 በሆድ ሳልሠራህ አውቄሃለሁ፥ ከማኅፀንም ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ፥ ለአሕዛብም ነቢይ አድርጌሃለሁ።

6 እኔም። ወዮ ጌታ እግዚአብሔር፥ እነሆ፥ ብላቴና ነኝና እናገር ዘንድ አላውቅም አልሁ።

7 እግዚአብሔር ግን እንዲህ አለኝ። ወደምሰድድህ ሁሉ ዘንድ ትሄዳለህና፥ የማዝዝህንም ሁሉ ትናገራለህና። ብላቴና ነኝ አትበል።

8 እኔ አድንህ ዘንድ ከአንተ ጋር ነኝና ከፊታቸው አትፍራ፥ ይላል እግዚአብሔር።"

{አስተውሉ 'የእግዚአብሔር ቃል ወደ ኤርሚያስ መጣ' ብሎ ከዚያ የእግዚአብሔር ቃል 'ይላል እግዚአብሔር' እያለ ይናገራል ማለት ነው? ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃልና እግዚአብሔር አንድ አካል አይደሉም ማለት ነው። ታዲያ የእግዚአብሔር ቃል እንዴት 'እግዚአብሔር ይላል፥' ብሎ ለኤርሚያስ የሚነግረው? ይህ የእግዚአብሔር ቃል ሌላ አካል ከሆነ ያን ጊዜ በዚህ ጥቅስ ውስጥ ሁለት አካላትን አገኘን ማለት ነው። ሁለቱም የማይለያዩ እንደመሆናቸው እግዚአብሔር ተብለዋል ፥ ከዚያ ደግሞ አንዱ በልዩ ስሙ 'እግዚአብሔር' አንዱ ደግሞ በልዩ ስሙ 'የእግዚአብሔር ቃል' ተብሏል። ከዚያ ደግሞ 'የእግዚአብሔር ቃል' ለኤርሚያስ 'በሆድ ሳልሠራህ ዐውቄሃለሁኝ' ብሎ ኤርምያስን የፈጠረው አምላክ እንደሆነ ራሱን ገለጠ። ስለዚህ 'እግዚአብሔር'ና 'የእግዚአብሔር ቃል' ሰውን የፈጠሩ ናቸው ማለት ነው። ቀድሞ በኢሳ 44 ፥ 24 ግን እኔ ብቻዬን ዓለምን ፈጠርሁኝ አላለንም እንዴ? ገና ሦስተኛ አካል አለ ፥ እስኪ እንመለከት።}

/ኢዮ 33 ፥ 4/

"4 የእግዚአብሔር መንፈስ ፈጠረኝ፥

ሁሉንም የሚችል የአምላክ እስትንፋስ ሕይወት ሰጠኝ።"

{እግዚአብሔርና የእግዚአብሔር ቃል ብቻ አልበረም ፥ የእግዚአብሔር መንፈስም ሰውን ፈጥሯል። ይህንን ነው ዘፍ 1 ፥ 26 "እግዚአብሔርም አለ፦ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር።" ያለው። እግዚአብሔር፣ የእግዚአብሔር ቃል፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ሰውን ፈጠሩ ፥ ሦስትና ሦስት ብቻ። ኢሳ 44 ፥ 24 ላይ ግን እኔ እግዚአብሔር ብቻዬን ፍጥረትን ፈጠርሁኝ ብሎ ነገረን። ሦስት አካላት አንድ ባሕርይ ማለት ይህ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ከእግዚአብሔር ስለሚገኝ ፥ የእግዚአብሔር መንፈስም ከእግዚአብሔር ስለሚሠርጽ ባሕርያቸው አንዲት ናት። እግዚአብሔር ፥ የእግዚአብሔር ቃል ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ፥ አንድ አምላክ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ደግሞ የለም ይላሉ። እንደዚያ ሲሉ እንስቅባቸዋለን። አሁን ይህ ጥቅስ እንዴት በብሉይ ኪዳን ውስጥ ምሥጢረ ሥላሴን እንደሚያሳይ አየን ፥ እስኪ ወደ ሐዲስ ኪዳን መጥተን የአምላካችን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት እነረጋግጥ።}

/ዮሐ 1 ፥ 3/

"3 ሁሉ በእርሱ ሆነ፥ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም።"

/ቆላ 1 ፥ 15 - 17/

"15-16 እርሱም የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው፤ የሚታዩትና የማይታዩትም፥ ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት፥ በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኵር ነው፤ ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል፤

17 እርሱም ከሁሉ በፊት ነው ሁሉም በእርሱ ተጋጥሞአል።"

{በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን ነገር እንደፈጠረ ነገረን። ስለዚህ እንደዚህ ጥቅስ ከሆነ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ዓለምን ፈጥሬያለሁኝ ያለው አምላክ ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስን ካጠናችሁት ፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ መሆኑን መካድ አትችሉም።}

5) ይወለዳል የተባለው ድንቅ አምላክ ነው።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚመጣው መሲህ አምላክ እንደሆነ ተነግሮናል። ይህንንም ደግሞ እስኪ እንመልከት፥

/ኢሳ 9 ፥ 6 - 7/

“6 ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።

7 ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም ድረስ በፍርድና በጽድቅ ያጸናውና ይደግፈው ዘንድ በዳዊት ዙፋንና በመንግሥቱ ላይ አለቅነቱ ይበዛል፥ ለሰላሙም ፍፃሜ የለውም። የእግዚአብሔር ቅንዓት ይህን ያደርጋል።”

{በኢሳይያስ ትንቢት ውስጥ ይህ ጥቅስ ኋላ ስለሚመጣው መሲህ የተነገረ ትንቢት ነው። ይህንን የሚያረጋግጡልንን ማስረጃዎች እንመልከት። በመጀመሪያ ለብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ትርጓሜን የሰጡ አይሁዳውያን ነበሩ። የመጀመሪያው ትርጓሜ ወደ አረማይክ ቋንቋ የተተረጐመው ‘ታርጉም’ የሚባለው መጽሐፍ ነው። እነዚህ መጻሕፍት ቃል በቃልም የዕብራይስጡን መጽሐፍ ቅዱስ ይተረጉማሉ ፥ ነገር ግን በተወሰኑ ቦታዎች ላይ አይሁዳውያን ያንን ጥቅስ እንዴት እንደተረዱትም ይገልጥልናል። ምክንያቱም አንዳንድ ጊዜ ቃል በቃል መመለስ ስለማይመች ትርጓሜ ይሰጠዋል። ከእነዚህ የታርጉም ሥራዎች መካከል አንዱ *Targum Jonathan ben Uzziel (ታርጉም ጆናታን ቤን ኡዚየል)* ይባላል። እስኪ ይህ ታርጉም ኢሳ 9 ፥ 6 ላይ ሲደርስ ምን እንደሚል እንመልከት፥

/Targum Jonathan Ben Uzziel on Isaiah 9:6/

“The prophet said to the house of David, For unto us a Child is born, unto us a Son is given, and He has taken the law uponHimself to keep it. His name is called from eternity, Wonderful, Mighty God, who liveth to eternity, The Messiah, whose peace shall be greatupon us in His days.”

/ነቢዩ ለዳዊት ቤት፥- ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና ይጠብቀውም ዘንድ ሕግን በራሱ ላይ ወሰደ። ስሙ ከዘላለም ጀምሮ ድንቅ፣ ኃያል አምላክ፣ እስከ ዘላለም የሚኖር፣ በዘመኑ ሰላሙ የሚበዛልን መሲህ ይባላል።/

[ስሙ እንዲህ ብሎ ይጠራል ብሎ ከነገረን በኋላ ደግሞ ‘መሲህ’ ይባላል ብሎ ይህ ጥቅስ የሚሆነው ለመሲሁ እንደሆነ ነገረን። ሌሎችም በዚህ ቃል ላይ ትርጓሜውን የሰጡ ሰዎች ስለመሲህ እንደሆነ ይናገራሉ። ገና ይህ አልበቃ ካለ ደግሞ ገና ከክርስትና መነሣት በኋላ የመጡ ክርስትናን የሚጠሉ የይሁዲ መምህራን መካከል እንኳን *Moses Maimonides (ሞሰስ ማይሞኒዲስ)* የሚባለው መምህር ይህንን ጥቅስ ለመሲህ ይጠቀመዋል። በየመን ውስጠዕ መሲህ ነኝ እያለ የተነሣ ሰው

ነበር ፥ ሞሰስ ማይሞነዲስ ይህንን ሰውዬ የሚከተሉትን ሰዎች ይህ መሲህ እንዳልሆነ ሊያሳያቸው እየጻፈላቸው ነው። እስኪ የሚለውን እንመልከት፥]

/Moses Maimonides/

“Do these characteristics make him a Messiah? You were beguiled by him because you have not considered the pre-eminence of the Messiah, the manner and place of his appearance, and the marks whereby he is to be identified. The Messiah, indeed, ranks after Moses in eminence and distinction, and God has bestowed some gifts upon him which he did not bestow upon Moses, as may be gathered from the verses: “His delight shall be in the fear of the Lord.” (Isaiah 11:3). “The Spirit of the Lord shall rest upon him. (11:2). “And Righteousness shall be the girdle of his loins.” (11:5). Six appellations were divinely conferred upon him as the following passage indicates: “For a child is born unto us, and a son is given to us, and the government is upon his shoulder, and he is called Pele, Yoetz, El, Gibbor, Abiad, Sar-Shalom.” (Isaiah 9:5). And another verse alluding to the Messiah is the following manner: “Thou art my son, this day have I begotten thee.” (Psalm 2:7). All these statements demonstrate the pre-eminence of the Messiah.”

/እነዚህ ባሕርያት መሲሕ ያደርጉታልን? የመሲሑን ታላቅነት፣ ቀደምትነት፣ የሚገለጥበትን መንገድና ቦታ፣ እንዲሁም የሚታወቅበትን ምልክቶች ስላላያችሁ በእርሱ ተታልላችኋል። መሲህ በእርግጥም ከሙሴ በኋላ በታላቅነት እና በልዩነት ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን እግዚአብሔርም ለሙሴ ያላደረጋቸውን አንዳንድ ስጦታዎች በርሱ አሳድሯል። ከጥቅሱ እንደተሰበሰበው፡- “ደስታው እግዚአብሔርን መፍራት ነው። (ኢሳይያስ 11፥3) “የእግዚአብሔር መንፈስ ያርፍበታል። (ኢሳ 11፥2) " ጽድቅም የወገቡ መታጠቂያ ይሆናል። (ኢሳ 11፥5) የሚከተለው ምንባብ እንደሚያመለክተው ስድስት መገለጫዎች በመለኮት ተሰጥተውታል፡- “ሕፃን ተወልዶልናልና ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ነው እርሱም ፔሌ፣ ዮውኤስ፣ ኤል፣ ጊቦር፣ አቢያድ፣ ሳር-ሻሎም ይባላል። ( ኢሳይያስ 9:5 ) እና ስለ መሲሑ የሚያመለክት ሌላ ጥቅስ የሚከተለው ነው፡- “አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወለድኩህ። (መዝሙረ ዳዊት 2:7) እነዚህ ሁሉ መግለጫዎች የመሲሑን ቀዳሚነትና ታላቅነት ያሳያሉ።/

[መሲሁ በምን ይታወቃል? ለሚለው ጥያቄ ሞሰስ ማይሞነዲስ ከጠቀሳቸው ጥቅሶች መካከል ኢሳ 9 ፥ 5 (በእኛዓ መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ኢሳ 9፥6) ይገኛል ማለት ነው። ጥቅሱ ውስጥ ስድስት ስሞች ለመሲሁ እንደተሰጠው ነገረን። እኒህም ስሞች የሚከተሉት ናቸው። እነርሱም ፥ ፔሌ (ድንቅ)፣ ዮውኤዝ (መካር)፣ ኤል (አምላክ)፣ ጊቦር (ኀያል)፣ አቢያድ (የዘለዓለም አባት)፣ ሳር-ሻሎም (የሰላም አለቃ) ናቸው። ስለዚህ እንደታላላቅ የይሁዲዎች መምህራንም መሠረት ይህ ጥቅስ ለመሲህ የሚነገር ጥቅስ ነው ማለት ነው።]

ገና ከአሁኑ የጌታችንን አምላክነት የሚያሳይ ጥቅስ እንደሆነ ትረዳላችሁ። ነገር ግን ይህንን ደግሞ ጥቅስ እንዴት ቅዱስ ማቴዎእ እንደሚያመጣው እንመልከተው። ቀድሞ በኢሳይያስ ትንቢት ውስጥ ኀይል አምላክ የሚባለው መሲህ እንደሚመጣ ተነግሯል አይደል? ‘አዎን’።}

/ማቴ 1 ፥ 23/

“23 እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኖአል፥ ትርጓሜውም፦ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚል ነው።”

{ኢሳይያስ ከ700 ዓመት በፊት አምላክ የሚባለው መሲሁ ይመጣል አለን። ያንን ደግሞ በጌታችን እንደተፈጠመ ሲያሳየን ሆን ብሎ ‘ዐማኑኤል’ የሚለውን ቃል ተርጐሞ አስቀመጠልን። ‘ዐማኑኤል’ ማለት ምን ማለት ነው? ‘እግዚአብሔር ከእኛ ጋር’ ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ‘ኀያል አምላክ’ ተብሎ አልነበር? ማቴዎስ ‘ከእኛ ጋር ሆነ’ ብሎ ትንቢቱን አገናኘው። ደግሞ እንዲሁ ሌላ አምላክ ነው የመጣው?

‘Ἰδοὺ ἡ παρθένος ἐν γαστρὶ ἕξει καὶ τέξεται υἱόν, καὶ καλέσουσιν τὸ ὄνομα αὐτοῦ Ἐμμανουήλ, ὅ ἐστιν μεθερμηνευόμενον Μεθ' ἡμῶν ὁ θεός.’ (ማቴ 1 ፥ 23 በግሪክ) /https://greekbible.com/matthew/1/23/

[በመጨረሻ ላይ ‘ὁ θεός’ የሚለውን ቃል ተመልከቱ። ‘ὁ θεός’ በአማርኛ ‘እግዚአብሔር’ ተተርጐሞ ያለው ነው። በእንግሊዘኛ ሲተረጐም ‘the God’ ይሆናል። ይህ ምን ለውጥ ያመጣል? ‘a God’ ቢል ኖሮ የሆነ አምላክ እንጂ የብሉይ ኪዳኑ አምላክ እንዳልሆነ ሊያመላክት ይችል ነበር። ‘the God’ ሲል ግን ያ የምታውቁት አምላክ የብሉይ ኪዳኑ አምላክ እንደሆነ ነገረን። ‘ዐማኑኤል’ ማለት በኢሳ 9፥6 ላይ ይመጣል የተባለው ድንቅ ኀያል አምላክ መጣ፣ ተወለደ፣ ከእኛ ጋር ሆነ ማለት ነው። ይህንን ዐይተው ጌታችንን ከክብሩ ለማዋረድ የሚለፉ ውሾች ይደነግጣሉ። እኛ በጌታችን ደስታ ሆነን ‘ቤዛ ኵሉ ዓለም ዮም ተወልደ’ እያልን ደስ እንሰኛለን። ነገሩ ግን በዚህ አላበቃም ፥ ማቴዎስ በጀመረበት ቃል ይጨርስልናል። በመጀመሪያ ‘እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ሆነ’ ብሎ ነበረ ፥ ያ እግዚአብሔር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ብሎ ደግሞ በማቴ 28 ፥ 20 ላይ ነግሮን በጀመረበት አጀማመር ወንጌሉን ፈጸመ።]

/ማቴ 28 ፥ 20/

“19-20 እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።”

[ወንጌሉን ሲጀምር ስለጌታችን ‘እግዚአብሔር ከእኛ ጋር’ እንደሆነ ነግሮን ነበር ፥ ያ ከእኛ ጋር የሆነው እግዚአብሔር ማን እንደሆነ ደግሞ ሲነግረን ደግሞ በማቴ 28፥20 ላይ ጌታችን ‘እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።’ ብሎ ነገረን። ማቴዎስ በጌታችን አምላክነት ጀመረ ፥ ከዚያም ደግሞ በጌታችን አምላክነት ደግሞ ፈጸመ። ማቴዎስ የጌታችንን አምላክነት እንዴት እንደሚያስተምር ተመለከታችሁ? ነገር ግን ለመጨረሻ እንዲሆንን የመጨረሻ ጥቅስን ከራእየ ዮሐንስ እናምጣ። በብሉይ ኪዳን ያ መሲህ ‘ኀያል አምላክ’ ተብሎ ነበር አይደል? ቅዱስ ዮሐንስ ደግሞ ጌታውን ምን ብሎ እንጠራው ተመልከቱ።]

/ራእ 1 ፥ 4 - 8/

“4 - 5 ዮሐንስ በእስያ ላሉት ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት፤ ካለውና ከነበረው ከሚመጣውም፥ በዙፋኑም ፊት ካሉት ከሰባቱ መናፍስት፥ ከታመነውም ምስክር ከሙታንም በኩር የምድርም ነገሥታት ገዥ ከሆነ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን። ለወደደን ከኃጢአታችንም በደሙ ላጠበን፥

6 መንግሥትም ለአምላኩና ለአባቱም ካህናት እንድንሆን ላደረገ፥ ለእርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ክብርና ኃይል ይሁን፤ አሜን።

7 እነሆ፥ ከደመና ጋር ይመጣል፤ ዓይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታል፥ የምድርም ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ። አዎን፥ አሜን።

8 <u>ያለውና የነበረው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ፦ አልፋና ዖሜጋ እኔ ነኝ ይላል።”</u>

[ ‘የወጉትም ሁሉ ያዩታል’ የተባለለት ራሱ ‘ያለውና የነበረው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ’ ነው። አምላካችን ጌታችን አፍቃሪያችን ሆይ ፥ እንወድሃለን እናፈቅርሃለን። ጌታችን ነህ ፥ ከአባትህና ሥጋን በመልበስህ አምላክህ ጋር ከሕይወትህ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የምትመሰገን አምላክ ሆይ ፥ አምላካችን ነህ። መዋትህ ሞተህ ተነሥተህ አሳይተኸናልና ዳግመኛም እንደምትመጣ እናምንሃለን ፥ ርግጠኞች ነን ትመጣለህ። መሐመድ በመንቀጥቀጥ ከፊት ሲቆም እናየዋለን፣ ሉተር በመንቀጥቀጥ ፊትህ ሲቆም እናየዋለን፣ ካልቪን በረዓድ አንተ ፊት ሲቆም እናየዋለን። እባክህን አምላካችን ከእነርሱ እንዳንሆን ጠብቀን ፥ የምንችለውን እንተጋለን የቀረውን መንገድ ተሸከምልን አምላካችን። ለአንተ በመታመናችን እንደምንድን እናውቃለን ፥ አሁንም ክብር ለአንተ ይሁን ምስጋና ለአንተ ይሁን አምልኮና አገዛዝ ለአንተ ይሁን። ለዘለዓለሙ አሜን።] }

6) ዘለዓለማዊው የብሉይ ኪዳን ፈራጁ እግዚአብሔር ነው።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር ብቻውን ዘለዓለማዊ እንደሆነ እንመለከታለን። እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ውስጥ ስለራሱ ‘እኔ የመጀመሪያና የመጨረሻ ነኝ’ ሲል እናገኘዋለን። ይህ ማለት በመጀመሪያም የነበርሁኝ ነኝ ፥ ከዚያም ደግሞ እስከመጨረሻውም እኖራለሁኝ ማለት ነው። ይህ አነጋገር ለእግዚአብሔር ብቻ እንጂ ለሌላ ሊሰጥ የማይችል ንግግር ነው። እስኪ በብሉይ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር እንዴት ራሱን እንደሚገልጥ እንደመልከት፥

/ኢሳ 44 ፥ 6 – 8/

“6 የእስራኤል ንጉሥ እግዚአብሔር፥ የሚቤዠም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እኔ ፊተኛ ነኝ እኔም ኋለኛ ነኝ፥ ከእኔ ሌላም አምላክ የለም።

7 እንደ እኔ ያለ ማን ነው? ይነሣና ይጥራ ይናገርም፤ ከጥንት የፈጠርሁትን ሕዝብ ያዘጋጅልኝ፥ የሚመጣውም ነገር ሳይደርስ ይንገሩኝ።

8 አትፍሩ አትደንግጡም፤ ከጥንቱ ጀምሬ አልነገርኋችሁምን? ወይስ አላሳየኋችሁምን? እናንተ ምስክሮቼ ናችሁ። ከእኔ ሌላ አምላክ አለን? አምባ የለም ማንንም አላውቅም።”

{ከእግዚአብሔር ውጪ የመጀመሪያና የመጨረሻ ሊሆን የሚችል አካል የለም። የመጀመሪያና መጨረሻ ማለት በመጀመሪያ የነበረ ከዚያም ደግሞ እስከመጨረሻውም ደግሞ የሚኖር ማለት ነው። ይህ ማለት በቀላል ዐማርኛ ዘለዓለማዊ ማለት ነው። ዘለዓለማዊ የሆነ ማንም ቢሆን ፍጡር ሊሆን አይችልም። እግዚአብሔር ብቻውን ነው ዘለዓለማዊ ሊሆን የሚችለው።}

/ራእ 1 ፥ 17/

“17 ባየሁትም ጊዜ እንደ ሞተ ሰው ሆኜ ከእግሩ በታች ወደቅሁ። ቀኙ እጁንም ጫነብኝ እንዲህም አለኝ፦ አትፍራ፤ **ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም** እኔ ነኝ።“

{ቅዱስ ዮሐንስ ሲያየው በፊቱ የወደቀው አካል እንዲህ ሲል ተናገረ። ‘የፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ’ ብሎ ተናገረ። በሌላ አነጋገር ዘለዓለማዊው እኔ ነኝ ብሎ ተናገረ። ይህ አካል ማን ሊሆን ይችላል? መቼም ይህ አካል እግዚአብሔር ብቻ ነው ሊሆን የሚችለው አይደል? ‘አዎን’ ስለዚህ ቀድሞ ኢሳ 44 ፥ 6-8 ላይ በብሉይ ኪዳን እንዳስተማረን ሁሉ በሐዲስ ኪዳንም አምላክ ‘የመጀመሪያና የመጨረሻ ነው’ አይደል? ‘አዎን’ በጀ እንግኢህ እስኪ ይህንን ጥቅስ እንቀጥለው፥

/ራእ 1 ፥ 18/

“18 ሞቼም ነበርሁ እነሆም፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ፥ የሞትና የሲኦልም መክፈቻ አለኝ።”

[መቼ ነበር እግዚአብሔር ሞቶ የሚያውቀው? መቼ ነው እግዚአብሔር ሞቶ የሚያውቀው? ቆይ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሞቶ ከዚያ በኋላ እስከዘለዓለም ድረስ ሕያው የሆነው ብቸኛው አካል ማን ነው? ‘ጌታችን’ የክብር ባለቤት ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ከላይ ዘለዓለማዊው አምላክ ነኝ ያለው ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ማለት ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ፊተኛውና መጨረሻው የሞተውና የተሣው ለዘለዓለምም የሚኖረው አምላክ ነው ማለት ነው። ለዚያ ተጨማሪ ደግሞ የሚከተሉትን ጥቅሶች መመልከት ይቻላል።] }

/ራእ 1 ፥ 7-8/

“7 እነሆ፥ ከደመና ጋር ይመጣል፤ ዓይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታል፥ የምድርም ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ። አዎን፥ አሜን።

8 ያለውና የነበረው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ፦ አልፋና ዖሜጋ እኔ ነኝ ይላል።”

/ዕብ 13 ፥ 8/

“8 ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው።“

{ጌታችን ዘለዓለማዊ የሆነው አምላካች እንደሆነ ፥ የብሉይ ኪዳኑ ያንን ቃል የተናገረው ራሱ እግዚአብሔር እንደሆነ ከእነዚህ ጥቅሶች በግልጥ መመልከት እንችላለን። ነገር ግን ዘለዓለማዊው አምላክ ብቻ አይደለም ፥ ለዘለዓለም የሚኖረው ዓለምን ሁሉ ዩፈርደው ራሱ አምላክ እንደሆነ ነገረን። ሰውን ሁሉ ሊፈርድ የሚችለው አምላካችን ራሱ እንደሆነ ደግሞ እናገኛለን። ይህንን ነገር ከዚህ ቦታ አብረን እንመልከተው።}

/መዝ 96 ፥ 10 – 13/

“10 በአሕዛብ መካከል፦ እግዚአብሔር ነገሠ በሉ። እንዳይናወጥም ዓለሙን እርሱ አጸናው፥ አሕዛብንም በቅንነት ይፈርዳል።

11 ሰማያት ደስ ይበላቸው፥ ምድርም ሐሤትን ታድርግ፤ ባሕርና ሞላዋ ይናወጡ፤

12 በረሃ በእርስዋም ያሉ ሁሉ ሐሤትን ያድርጉ፤ የዱር ዛፎች ሁሉ በዚያን ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ደስ ይላቸዋል፤

13 ይመጣልና፤ በምድር ላይ ሊፈርድ ይመጣልና፤ እርሱም ዓለምን በጽድቅ አሕዛብንም በቅንነት ይፈርዳል።“

/መዝ 98 ፥ 5 - 9/

“5 ለእግዚአብሔር በመሰንቆ፥ በመሰንቆና በዝማሬ ድምፅ ዘምሩ።

6 በዋሽንትና በመለከት ድምፅ በንጉሥ በእግዚአብሔር ፊት እልል በሉ።

7 ባሕርና ሞላዋ፥ ዓለምም በእርስዋም የሚኖሩ ይናወጡ።

8 ወንዞችም በአንድነት በእጅ ያጨብጭቡ፤ ተራሮች ደስ ይበላቸው፥ በምድር ሊፈርድ ይመጣልና።

9 ለዓለምም በጽድቅ ለአሕዛብም በቅንነት ይፈርዳል።”

{ቅዱስ ዳዊት ምን ዐይነት ቋንቋ እየተጠቀመ እንደሆነ ተመልከቱ። ‘በእግዚአብሔር ፊት እልል በሉ ፥ ይመጣል፣ በቅንነት ለዓለም ይፈርዳል’ እያለ ቅዱስ ዳዊት ታላቅ ድምፅ እየተናገረን ነው። እየመጣ ያለው እግዚአብሔር ራሱ እንደሆነ ደግሞ አጠናክሮ የሚነገረን ‘ባሕርና ዓለም በሙሉ ይናወጡ፣ ወንዞች ያጨብጭቡ፣ ተራሮች ደስ ይበላቸው’ እያለ ቅዱስ ዳዊት እየደጋገመ በመናገሩ ነው። ራሱ የፈጠራቸው እግዚአብሔር ማን ሊሆን ይችላል ባሕርና ዓለም ሁሉ እንዲህ የሚናወጡለት? አምላካችን ካልሆነ ማን ሊሆን ይችላል ወንዞች የሚያጨበጭቡለት? ፈጣሪያችን ካልሆነ በቀር ማን ነው ተራሮች ደስ የሚሰኙለት? ከዚያ አስቀጥሎ ምን አለን? ያ እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ እንደሥራው ሊሰጠው ይመጣል ፥ ለእያንዳንዱ ሊፈርድ ይመጣል። አሁን አስተውሉ ‘ማን ነው ሊፈርድ የሚመጣው?’ ፥ አምላካችን ፈጣሪያችን ራሱ ነው።}

/ማቴ 25 ፥ 31 - 32/

“31 የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላእክቱ ሁሉ፥ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል፤

32 አሕዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፤ እረኛም በጎቹን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በርሳቸው ይለያቸዋል፥”

{በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሰዎችን ሁሉ ይፈርዳል የተባለው እግዚአብሔር ነበር። ሐዲስ ኪዳን ያ ይፈርዳል የተባለው ይመጣል የተባለው ጌታችን ‘እኔ ነኝ’ ብሎ ተናገረ። በመጨረሻ ይመጣል የተባለው እግዚአብሔር ራሱ ጌታችን የክብር ባለቤት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ‘እግዚአብሔር በጌታችን በኩል ነው የሚፈርደው’ ቢሉ አንደኛ መዝ 96 እና 98 ላይ ይመጣል የተባለው ሌላ አካል አይደለም ፥ ራሱ እግዚአብሔር ነው እንጂ ሌላ አካል ነው አልተባለም። ስለዚህ ይመጣል የተባለው አካል ራሱ እግዚአብሔር ነው እንጂ ሌላ አካል አይደለም። ነገሩን እስኪ ገና እናጽንነው።}

/ራእ 22 ፥ 12 – 21/

“12 **እነሆ፥ በቶሎ እመጣለሁ፥ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ።**

13 **አልፋና ዖሜጋ፥ ፊተኛውና ኋለኛው፥ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ።**

14 ወደ ሕይወት ዛፍ ለመድረስ ሥልጣን እንዲኖራቸው በደጆችዋም ወደ ከተማይቱም እንዲገቡ ልብሳቸውን የሚያጥቡ ብፁዓን ናቸው።

15 ውሻዎችና አስማተኞች ሴሰኛዎችም ነፍሰ ገዳዮችም ጣዖትንም የሚያመልኩት ውሸትንም የሚወዱና የሚያደርጉ ሁሉ በውጭ አሉ።

16 **እኔ ኢየሱስ በአብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ይህን እንዲመሰክርላችሁ መልአኬን ላክሁ። እኔ የዳዊት ሥርና ዘር ነኝ፥ የሚያበራም የንጋት ኮከብ ነኝ።**

17 መንፈሱና ሙሽራይቱም፦ ና ይላሉ። የሚሰማም፦ ና ይበል። የተጠማም ይምጣ፥ የወደደም የሕይወትን ውኃ እንዲያው ይውሰድ።

18 በዚህ መጽሐፍ የተጻፈውን የትንቢት ቃል ለሚሰማ ሁሉ እኔ እመሰክራለሁ፤ ማንም በዚህ ላይ አንዳች ቢጨምር እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ የተጻፉትን መቅሠፍቶች ይጨምርበታል፤

19 ማንምም በዚህ በትንቢት መጽሐፍ ከተጻፉት ቃሎች አንዳች ቢያጎድል፥ በዚህ መጽሐፍ ከተጻፉት ከሕይወት ዛፍና ከቅድስቲቱ ከተማ እግዚአብሔር ዕድሉን ያጎድልበታል።

20 **ይህን የሚመሰክር፦ አዎን፥ በቶሎ እመጣለሁ ይላል። አሜን፥ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ ና።**

21 የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችን ጋር ይሁን፤ አሜን።”

{ጌታችን ራሱ ‘እኔ አልፋና ዖሜጋ፣ ፊተኛውና ኋለኛው፣ የመጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ። ለእያንዳንዱም የዋጋውን የምሰጠው እኔ ነኝ’ ብሎ ያ የሚፈርደው አምላክ የብሉይ ኪዳኑ አምላክ እኔ ነኝ ብሎ ነገረን። ‘አልፋ’ የመጀመሪያው የግሪክ ፊደል ነው ፥ ‘ዖሜጋ’ ደግሞ የመጨረሻው የግሪክ ቃል ነው። በዐማርኛ ቢሆን ‘ሀ እና ፐ’ እንደማለት ነው። ቅዱስ ዮሐንስም ጌታችን ‘ቶሎ እመጣለሁኝ’ ሲል ‘አሜን ፥ ጌታ ኢየሱስ ሆይ ና’ ብሎ ለጌታችን መለሰለት። አሜን ፥ ጌታችን ሆይ ና ፥ ማራናታ አምላካችን ሆይ ና። ማራናታ ጌታችን ሆይ ና። አንተ የዘለዓለም አምላካችን ነህና።}

7) ፍጥረታት ሁሉ ከአባቱ ጋር እኩል የሚያመልኩት አምላክ ነው

/ራእ 5 ፥ 12 - 13/

“12 በታላቅም ድምፅ፦ የታረደው በግ ኃይልና ባለ ጠግነት ጥበብም ብርታትም ክብርም ምስጋናም በረከትም ሊቀበል ይገባዋል አሉ።

13 በሰማይና በምድርም ከምድርም በታች በባሕርም ላይ ያለ ፍጥረት ሁሉ በእነርሱም ውስጥ ያለ ሁሉ፦ በረከትና ክብር ምስጋናም ኃይልም ከዘላለም እስከ ዘላለም በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው፥ ለበጉም ይሁን ሲሉ ሰማሁ።”

{ቅዱስ ዮሐንስ የሚችለውን ሁሉ ቋንቋ ጨረሰው ፥ አስተውሉ! በሰማይና በምድርም፣ ከምድርም በታች በባሕፍርም ላይ ያለ ፍጥረት፣ በእርሱም ውስጥ ያሉ' ብሎ ቋንቋውን በሙሉ ጨረሰ። ስለዚህ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ በዚህ ጥቅስ ውስጥ ያስቀረው ፍጥረት የለም። በሰማይም ቢሆን በምድርም ቢሆን በባሕርም ቢሆን በየትኛውም ቦታ ቢሆን ያሉ ፍጥረታትን ሁሉ ጠቅልሎ ተናገረ። ይህንን የቅዱስ ዮሐንስ የቋንቋ አጠቃቀም ከተረዳን በኋላ ፍጥረታት በሙሉ ምን እያሉ እንደሆነ እንመልከት። ' ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ፥ **ለበጉም ይሁን**' አሉ። ምን???!!! ስለዚህ ቅዱስ ዮሐንስ ቀድሞ ፍጥረታትን በሙሉ ጠቅልሎ ከተናገረ እዚህ ጋር 'በጉ' ከፍጥረታት ወገን አይደለም ማለት ነው። ደግሞም አስተውሉ ፥ በዙፋን ላይ ለተቀመጠው ማለትም ለአብ ክብር፣ ሞገስ እያሉ ፍጥረታት በሙሉ ያመሰግኑታል ፥ ነገር ግን ለእርሱ ብቻ አይደለም። ከእርሱ ጋር በዙፋን ላይ ላለውም ለበጉም ተመሳሳይ ምስጋናን ያቀርቡለታል። በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለእርሱ ክብር፣ ስግደት፣ አገዛዝ ይገባል እንደሚሉት በተመሳሳይ መንገድ ለበጉም ክብር፣ ሞገስ፣ ስግደት ይገባል እያሉ ይናገራሉ ማለት ነው። በጉ ፍጡር ሊሆን አይችልም ማለት ነው ፥ ከአብ ጋር አንድ ምስጋናን አንድ አምልኮን የሚቀበል አምላክ ነው ማለት ነው። በርግጥ ከሰዎች ጋር ብዙ አያከራክርም ነገር ግን ለምኑም 'በጉ' ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ በቀላሉ ማሳየት ይቻላል። እስኪ እነኚህን ጥቅሶች እንመልከት፥}

/1ኛ ጴጥ 1 ፥ 1-2/

"1-2 የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ጴጥሮስ፥ እግዚአብሔር አብ አስቀድሞ እንዳወቃቸው በመንፈስም እንደሚቀደሱ፥ ይታዘዙና በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ይረጩ ዘንድ ለተመረጡት በጳንጦስና በገላትያ በቀጰዶቅያም በእስያም በቢታንያም ለተበተኑ መጻተኞች፤ ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ።"

{ቅዱስ ጴጥሮስ የማን ሐዋርያ ነው? ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት በማን የተመረጡ ሐዋርያት ናቸው? የማን ሐዋርያት ይባላሉ? የጌታችን የክብር ባለቤት የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት ናቸው። እሺ ፥ ቅዱስ ዮሐንስ ደግሞ እኒህ ሐዋርየዓት የማን ሐዋርያት እንደሆኑ እንደሚነግረን ተመልከቱ፥}

/ራእ 21 ፥ 14/

"14 ለከተማይቱም ቅጥር አሥራ ሁለት መሠረቶች ነበሩአት፥ በእነርሱም ውስጥ የአሥራ ሁለቱ የበጉ ሐዋርያት ስሞች ተጽፈው ነበር።"

{ዐሥራ ሁለቱ የማን ሐዋርያት ናቸው? የበጉ ሐዋርያት ተብለው ተጠሩ ፥ በዚህ የቅዱስ ዮሐንስ ንግግር በጉ ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ገለጠልን ማለት ነው። ዳግመኛም ደግሞ ቅዱስ ዮሐንስ ኋላ በራእዩ እንደሚጠቅሰው ሲያዘጋጀን በወንጌሉ ላይ ጌታችንን ምን ብሎ እንደጠራው እንመልከት፥}

/ዮሐ 1 ፥ 29/

"29 በነገው ዮሐንስ ኢየሱስን ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ እንዲህ አለ፦ እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ።"

{ስለዚህ ምንም ጥርጥር የለንም ቅዱስ ዮሐንስ 'በጉ' ሲል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እየተናገረ እንደሆነ። ከዚያ ሲቀጥል ደግሞ ራእ 19 – 21 ያለውንም አንብቡ ራሱ በጉ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚባል፣ ራሱም ደግሞ ጌታችን ኢየሱስ

ክርስቶስ እንደሆነ በቀላሉ ይነግረናል። እንደዚያ ካልን ግን ያ ከእግዚአብሔር አብ ጋር እኩል የሚመለከው ከፍጥረታት ሁሉ ልዩ የሆነው አምላክ ራሱ ጌታችን አምላካችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።}

8) ስሙን በአምላክነት የምንጠራው አምላካችን ነው።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሰዎች ለእግዚአብሔር ብቻ 'ነፍሴን እሰጣለሁኝ' እያሉ ሲናገሩ እንመለከታለን። አንድም ቦታ ቢሆን ለፍጡር ይህንን ሲናገሩ አናገኝም። አምላኬ ሆይ ፥ ነፍሴን ተቀበል እያሉ ለእግዚአብሔር የሚናገሩት እግዚአብሔር ባለቤቷ እንደሆነ ሲያመላክቱ ነው።

/መዝ 31 ፥ 5/

"5 በእጅህ ነፍሴን እሰጣለሁ፤ የእውነት አምላክ አቤቱ፥ ተቤዠተኸኛል።"

/መዝ 99 ፥ 5 – 7/

"5 አምላካችንን እግዚአብሔርን ከፍ ከፍ አድርጉት፥ ቅዱስ ነውና ወደ እግሩ መረገጫ ስገዱ።

6 ሙሴና አሮን በካህናቱ ዘንድ፥ ሳሙኤልም ስሙን በሚጠሩት ዘንድ ናቸው፤ እግዚአብሔርን ጠሩት፥ እርሱም መለሰላቸው።

7 በደመና ዓምድም ተናገራቸው፤ ምስክሩንና የሰጣቸውን ትእዛዝ ጠበቁ።"

{ከዚያ ግን በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ራሱን ንግግር ለጌታችን ለክብር ባለቤት ለኢየሱስ ክርስቶስ ሲናገረው እንመለከተዋለን። ጌታችን ፍጡር ከሆነ እንዲህ ዐይነት ንግግር እግዚአብሔርን መስደብ ነው የሚሆነው። ጌታችን ግን የብሉይ ኪዳኑ አምላክ በመሆኑ ይህ አምልኮ የሚገባው እግዚአብሔር ነው።}

/ሐዋ 7 ፥ 58 - 60/

"58 ከከተማም ወደ ውጭ አውጥተው ወገሩት። ምስክሮችም ልብሳቸውን ሳውል በሚሉት በአንድ ጎበዝ እግር አጠገብ አኖሩ።

59 እስጢፋኖስም፦ <u>**ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ ነፍሴን ተቀበል ብሎ ሲጠራ ይወግሩት ነበር**</u>።

60 ተንበርክኮም፦ ጌታ ሆይ፥ ይህን ኃጢአት አትቍጠርባቸው ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ። ይህንም ብሎ አንቀላፋ። ሳውልም በእርሱ መገደል ተስማምቶ ነበር።"

/1ኛ ቆሮ 1 ፥ 2/

"2 በቆሮንቶስ ላለች ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን፥ በክርስቶስ ኢየሱስ ለተቀደሱት፥ የእነርሱና የእኛ ጌታ የሆነውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም በየስፍራው ከሚጠሩት ሁሉ ጋር ቅዱሳን ለመሆን ለተጠሩት፤"

{ጌታችን በእውነት ወደእርሱ የምንሄድ ወደእርሱ የምንጠራ ፥ ስንሞትም ነፍሳችን የእርሱ የሆነች አምላካችን ነው። አምላካችን ሆይ ክብር ይገባሃል ፥ ስንሞት ለእጅህ አታውጣል። አንተ ነፍሳችንን ተቀበል ፥ ከአንተ ጋር ለመኖር አብቃን።}

9) ቤተ ክርስቲያኒቱን በደሙ የመሠረታት ሁሉን ያስገኘ እግዚአብሔር ነው።

/ሐዋ 20 ፥ 28/

“28 በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ።”

{የእግዚአብሔር ደም? እግዚአብሔር ደም አለው? ምን ማለት ነው? በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ደሙን ያፈሰሰው እግዚአብሔር ማን ነው? ‘አዎን’ ጌታችን አምላካችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ለዚያ ነው ተዋሕዶ ብለን የምናምነው ፥ ለዚያ ነው አንዱ እግዚአብሔር ሞተ፣ አንዱ እግዚአብሔር በደሙ ቤተ ክርስቲያኒቱን ገዛት እያልን የምናምነው። ይህንን ጥቅስ ማምለጥ አይቻልም ፥ ጌታችን ራሱ ደሙን አፍስሶ ቤተ ክርስቲያኒቱን የገዛት እግዚአብሔር ነው። ይህንን ጥቅስ የጌታችንን አምላክነት በቀላሉ ለማሳየት መጠቀም ትችላላችሁ ፥ ይህ አስተምህሮ በጣም ቀላል ነው።}

/1ኛ ቆሮ 8 ፥ 5 - 6/

“5 መቼም ብዙ አማልክትና ብዙ ጌቶች አሉ፤ ነገር ግን በሰማይ ሆነ በምድርም ሆነ አማልክት የተባሉ ምንም ቢኖሩ፥

6 ለእኛስ ነገር ሁሉ ከእርሱ የሆነ እኛም ለእርሱ የሆንን አንድ አምላክ አብ አለን፥ ነገር ሁሉም በእርሱ በኩል የሆነ እኛም በእርሱ በኩል የሆንን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን።”

{ከላይ ብዙ አማልክትና ብዙ ጌቶች አሉ ሲል ቅዱስ ጳውሎስ እያስተላለፈ ያለውን መልእክት አስተውሉ። ‘አማልክትና ጌቶች’ ሲባሉ ለአምልኮ ነው። ሰዎች ‘ጌቶች’ እያሉ ያመልኳቸው የነበሩትን አካላት ነው እየጠቀሰ ያለው። ይህንን ነጥብ ከላይ ከቁጥር 3 ጀምሮ ስለአምልኮ እየተናገረ በመሆኑ መገንዘብ እንችላለን። ከዚያ ቀጥሎ ግን ‘እነርሱ እንዲህ ያምናሉ ፥ እኛ ግን’ ብሎ የብሉይ ኪዳኑን የአይሁዳውያን የእምነት ቃል ተናገረው። የብሉይ ኪዳን ዋነኛ መሠረት የሆነውን ቃል መልሶ በሐዲስ ኪዳን አስፍቶ ተናገረው። ያ የብሉይ ኪዳን ቃል ዘዳ 6 ፥ 4 ላይ ይገኛል። እንዲህም ይላል፥

/ዘዳ 6 ፥ 4/

“4 እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው።”

[ይህንን ወስዶ ቅዱስ ጳውሎስ ‘እኛም ለእርሱ የሆንን አንድ አምላክ አብ አለን፥ ነገር ሁሉም በእርሱ በኩል የሆነ እኛም በእርሱ በኩል የሆንን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን።’ ብሎ አስፍቶ አልምቶ ተናገረው። አንድ አምላክ አብ አለን ብሎ የአብን አምላክነት ነገረን። ከዚያ ደግሞ ቀድመን ‘ጌቶች’ ያላቸውን በአምላክነት እየተመለከቷቸው ነው ብሎ እኛ ግን ‘አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ’ አለን ብሎ እርሱም አምላካችን እንደሆነ ነገረን። አስተውሉ እንዴት ቅዱስ ጳውሎስ እንዳነጻጸረው። ‘አማልክት’ እያሉ ጣዖታትን ያመልካሉ ፥ እኛ ግን አንድ አምላክ እግዚአብሔር አለን። ‘ጌቶች’ እያሉ

ጣዖታትን በአምልኮ በተገዢነት ይምለከታሉ ፥ እኛ ግን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን። ይህንን ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ የብሉይ ኪዳኑን አስፍቶ ተናገረን። ደግሞም ሌላም ማስረጃ እናምጣ ለዚህ ቃል፥]

በብሉይ ኪዳን ውስጥ በዕብራይስጡ ቃል ‘ኤሎሂም’ (Elohim) አምላክ ለሚለው ቃል ሲያገለግል እንመለከታለን። ‘ያህዌህ’ (Yahweh) የሚለው ቃል ደግሞ ለብሉይ ኪዳኑ እግዚአብሔር ልዩ ስሙ ነው። ይህ ስም ለየትኛውም ፍጡር ወይም ለሌላ ለየትኛውም አምላክ አይሰጥም። ይህ ስም ለእውነተኛው አንድ አምላክ ብቻ የሚሰጥ ስም ነው። ለዘመናት አይሁዳውያን የዕብራይስጥን ቋንቋ ይጠቀሙ ነበር። ከዘመናት በኋላ ግን ግሪክ የዓለም በነጋገሪያ ቋንቋ ሲሆን አይሁዳውያን ያንን ቋንቋ እየለመዱ ፥ የዕብራይስጡን ጥንታቸውን እየተዉ ሄደዋል። ለዚያም ነበር የሰብዓ ሊቃውንት ትርጓሜ (Septuagint) በአይሁዳውያን ዘንድ በጣም በአገልግሎት ውስጥ ይውል የነበረው። በዕብራይስጡ ውስጥ ‘ያህዌህ’ የሚሉትን ቦታዎች ሁሉ ወደ ግሪኩ ሲተረጐሙ ‘ኪሪዩስ’ (κύριος) ተብለው ነው የሚተረጐሙት። ‘ኪሪዩስ’ ማለት ‘ጌታ’ ማለት ነው ፥ አንድ አይሁዳዊ ‘አንድ ጌታ’ ነው ያለኝ ብሎ በግሪክ ሲጽፍ ከእግዚአብሔር በቀር ሊሆን አይችልም። አሁን ይህንን ይዤ ወደየት እየሄድሁኝ እንደሆነ የምታውቁት ይመስለኛል።

ብሉይ ኪዳንን እንደእጁ ጀርባ የሚያውቀው የግሪክ ቋንቋን እየተናገረና መልእክቱንም በግሪክ ቋንቋ እየጻፈ ያለው ቅዱስ ጳውሎስ ‘θεός’ (አምላክ) ብሎ ለእግዚአብሔር አብ ነገረን ፥ እርሱ የብሉይ ኪዳኑ ‘ኤሎሂም’ (አምላክ) ነው ሲል። ጌታችንን ደግሞ ለፍጡር የማይሰጠውን ‘አንድ ጌታ’ ብሎ ያ የብሉይ ኪዳኑ ‘ያህዌህ’ እንደሆነ አመላከተን። ቅዱስ ጳውሎስ ‘አንድ ጌታ’ ብሎ ስለጌታችን ሲናገር በግልጥ ለሚሰሙት ሰዎች ጌታችን ‘ያህዌህ’ ነው እያላቸው ነው ማለት ነው። ያ የብሉይ ኪዳኑ አምላክ ዓለምን ሁሉ ያስገኘው አምላክ እርሱ ነው ፥ አንድ እውነተኛው አምላክ እርሱ ነው ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ መሰከረልን ማለት ነው።}

10) የእኛ ፍጹም አምላክ እየተባለ ተጠርቷል

ጌታችን አምላካችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ መሆኑን በሐዲስ ኪዳን ውስጥ እንመለከተዋለን።

/ሮሜ 9 ፥ 5/

“5 አባቶችም ለእነርሱ ናቸውና፤ ከእነርሱም ክርስቶስ በሥጋ መጣ፥ <u>እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም የተባረከ አምላክ ነው፤ አሜን</u>።”

/ቲቶ 2 ፥ 12 - 13/

“12-13 ይህም ጸጋ፥ ኃጢአተኛነትንና ዓለማዊን ምኞት ክደን፥ የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን <u>የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን</u> ክብር መገለጥ እየጠበቅን፥ ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል።”

/2ኛ ጴጥ 1፥1/

“1 የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያና ሐዋርያ የሆነ ስምዖን ጴጥሮስ፥ <u>በአምላካችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ</u> ጽድቅ ካገኘነው ጋር የተካከለ የክብር እምነትን ላገኙ።”

/ዮሐ 20 ፥ 28/

“28 ቶማስም፦ **ጌታዬ አምላኬም** ብሎ መለሰለት።”

/ኢሳ 9 ፥ 6/

“6 ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ **የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል**።”

አምላካችን ሆይ እንወድሃለን፣ ቅዱሳንህንም አንተን ስለምንወድህ እንወዳቸዋለን። አምላካችን ሆይ ፥ አንተን ከዘለዓለማዊ ክብርህ ለማውረድ የሚሞክሩትን ውሾች ሁሉ አፋቸውን እንድንዘጋ ኀይልን ስጠን። ከአንተ ጋር እንድንኖር ርዳን ፥ ፍቅራችን ነህ። እኛ ስምህን ለማግነን እንፈልጋለን ፥ አቤቱ እኛ አናስፈልግህም፣ አንተ ግን ታስፈልገናለህ። የሚጣፍጠውን ስምህን ማግነን ወታደሮች እንድንሆን ከፊትህ ቆመናልና። እንወድሃለን፣ እናፈቅርሃለን፣ ለዘለዓለምም እናከብርሃለን። አሜን።

**አስጀምሮ ላስፈጸመ ለልዑል እግዚአብሔር ክብር እና ምሥጋና ይኹን። ክርስቶስ ተነሥቷል በእውነት ተነሥቷል**

**ኪርያላይሶን እግዚአብሔር አብ ሆይ ማረን ፥ ኪርያላይሶን እግዚአብሔር ወልድ ሆይ ማረን ፥ ኪርያላይሶን እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሆይ ማረን።  ማራናታ ፥ ጌታ ሆይ አትዘግይ ቶሎ ና።**

**ወስብሐት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር ለዓለመ ዓለም አሜን**